ርዕሰ ጉዳይ-የምርጫውን ሞዴል ማስተዋወቅ፡ የኮርስ ቁሳቁሶችን ለማግኘት ቀላሉ መንገድ

ሰላምታ, ራፕተሮች!

በ2026 የስፕሪንግ ሴሚስተር መጀመሪያ ላይ፣ ሞንትጎመሪ ኮሌጅ ሁሉንም በአስተማሪ የሚፈለጉ የኮርስ ቁሳቁሶችን (ለምሳሌ የመማሪያ መጽሀፍት፣ የስነ ጥበብ አቅርቦቶች፣ወዘተ) በአጋራችን በSlingshot የተጎላበተ አዲስ የማድረስ ስርዓት ያቀርባል። ይህ አገልግሎት በመጀመሪያ ቀን የሚፈልጉትን ሁሉ ለማግኘት ቀላል ያደርገዋል!
ለስፕሪንግ ሴሚስተር ሲመዘገቡ ማወቅ ያለብዎት ነገር ይኸውና፣
በ Slingshot Choice ውስጥ ይመዘገባሉ። ሁሉም አስፈላጊ ቁሳቁሶች ወደ ሮክቪል ካምፓስ ማከማቻ ይደርሳሉ።
የመፅሐፎችን ወይም የሚያዙትን ማንኛውንም የትምሕርት መገልገያ ቁሶች የሚላክበትን አድራሻ በSlingshot ፖርታል ማስመዝገብ ይችላሉ።
ይህንን ምርጫ መጠቀም ለምን አስፈለገ?
· ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ በመማር ላይ እንዲያተኩሩ
· ትምህርቶች ከመጀመራቸው በፊት የኮርስዎን እቃዎች እንዲያዘጋጁ

· ጊዜ እንዲቆጥቡ እና ጭንቀትን እንዲቀንሱ
· አስተማሪዎ የሚፈለጉትን የኮርስ ቁሳቁሶች ወደ እርስዎ እንዲልኩ - ወይም - ካምፓስ ተገኝተው እንዲረከቡ ይረዳዎታል።

ለኮርሱ ቁሳቁሶች  የሂሳብ አከፋፈል ማቅለያ መንገድ፣
ሂሳቡ በቀጥታ በተማሪው አካውንት እንዲመዘገብ የሚያደርግ ሲሆን አስፈላጊ ከሆነ በፋይናንሺያል እርዳታ መጽሐፍ ቫውቸሮች ሊሸፈኑ ይችላሉ። የኮርስዎን ቁሳቁሶች ለማየት እና ለመክፈል ዝርዝሮችን ለማግኘት የክፍያዎችን ድረ-ገጽ ይጎብኙ።
በራስዎ መግዛትን ይመርጣሉ?
ከፈለጉ ከዚህ አማራጭ ውስጥ ራሶን ማውጣት ይችላሉ ነገር ግን ከዚህ ፖርታል ራስዎን ካስወጡ ወይም ምርጫውን ከሰረዙ ሁሉንም የኮርስ ቁሳቁሶችን በራስዎ የማግኘት እና የመግዛት ሃላፊነት አለብዎት ማለት ነው።
አስፈላጊ ቀናቶች፣
ኦክቶበር 27፣ 2025፡ የተማሪ ፖርታል ለግምገማ እና ለምርጫ ለውጦች ክፍት ነው።
ጃንዋሪ 9፣ 2026፡ ለውጦችን ለማድረግ ወይም ከፖርታሉ ራስን ለማስወጣት የመጨረሻ ቀን ነው።

ፌብሩዋሪ 2፣ 2026፡ በማንኛውም ምክንያት ለ100% ተመላሽ ገንዘብ የመጨረሻ ቀን። *በ add/drop ወቅት በማንኛውም ምክንያት ለተሰረዙ ኮርሶች፣ ተማሪዎች በ7 ቀናት ውስጥ 100% ተመላሽ ገንዘብ ሊያገኙ ይችላሉ።

ቀጥሎ ምን አለ?

ለስፕሪንግ ሴሚስተር ከተመዘገቡ፣ ዝርዝር መረጃዎችን የያዘ ኢሜል ከSlingshot ይደርስዎታል።

ተጨማሪ እገዛ ይፈልጋሉ?

ለስራ ሰአታት፣ ተደጋጋሚ ጥያቄዎች እና የድጋፍ መርጃዎች የMC Campus Store ድረ-ገጽን ይጎብኙ። በተጨማሪም በ montgomerycollege@slingshot.edu ኢሜይል ይላኩ ወይም በስልክ ቁጥር 240-567-5302 ይደውሉ።

የ 2026 የስፕሪንግ ሴሚስተርን ከትክክለኛው የኮርስ ቁሳቁሶች በመጀመር ስኬታማ እናድርገው።

የሞንትጎመሪ ኮሌጅ ረዳት ኢንተርፕራይዞች